# እየተስፋፋ የሚሄድ ደስታ

ሉቃ 24፡1-12፣ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን (ዕሑድ ዕለት) መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣ የያዕቆብ እናት ማርያም ከሌሎች ሴቶች ጋር ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው እጅግ ማለዳ ሳለ ወደ መቃብሩ ሄዱ። ድንጋዩ ከመቃብሩ ተንከባልሎ ስላገኙት ውስጥ ዘልቀው ቢገቡም የጌታ ሥጋ በዚያ አልነበረም። በሁኔታው ግራ ተጋብተው ሳሉ በድንገት እጅግ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ተገልጠውላቸው፣ ጌታ ኢየሱስ ከሙታን መነሳቱን ነገሩዋቸው። ሴቶቹ ከመቃብሩ ሥፍራ ተመልሰው ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ ለአስራ አንዱና ለተቀሩት ሁሉ ነገሯቸው። ሆኖም እነርሱ ሴቶቹ የተናገሩት ቃል አላመኑዋቸውም። ጴጥሮስ ግን ሮጦ መቃብሩ ጋ ደርሶ ወደ ውስጡ ሲመለከት የጌታ ሥጋ በዚያ አለመኖሩንና በፍታው ብቻ ውስጥ ተቀምጦ ስላየ እየተገረመ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ሉቃ 24፡13-35፤ በዚሁ ቀን ከደቀ-መዛሙርቱ ሁለቱ ከኢየሩሳሌም 11 ኪ/ሜትር ወደሚርቅ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር። እነርሱም ስለ ሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር። በዚሁ ሁኔታ ሳሉ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ጀመር። ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር። በሌሎች ለሐዋሪያትና ለማግደላዊት ማርያም በተገለጠባቸው ስፍራዎችም እርሱ መሆኑን ማብራሪያ ሳይነግራቸው ልክ እንዳዩት ወዲያውኑ አላወቁትም ነበር። (ሉቃ 24፡36-40፣ዮሐ 20፡14-16)

ሉቃ 24፡16፣ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የ2005 እትም እንዲህ ብሎ ተርጉሞታል። "በዓይናቸው እያዩት ማን እንደሆነ ማወቅ አልቻሉም።"

እርሱም "እየሄዳችሁ መንገድ ላይ እርስ በርስ እንዲህ የምትወያዩት ምንድን ነው?" አላቸው። እነርሱም በሐዘን ክው ብለው (ልባቸው ተሰብሮ/በሀዘን ተሞልተው) ቆሙ። ከእነርሱም አንዱ ቀለዮጳ የተባለው በእነዚህ ቀናት በኢየሩሳሌም የሆነው ነገር አንተ ያላወቅኸው ለአገሩ እንግዳ ነህን? ሲል መለሰለት።

ሉቃስ 24፡19-21፣ እርሱም፣ "የሆነው ነገር ምንድን ነው?" አላቸው። እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፤[20] እርሱን **የካህናት አለቆችና ገዦቻችን ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሰጡት፤ ሰቀሉትም።** [21] እኛ ግን እስራኤልን ይቤዢል ብለን ተስፋ ያደረግነው እርሱን ነበር፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።

ከሉቃ 24፡14-19፣ ባለው ክፍል ውስጥ "ስለ ሆነው ነገር" የሚለው ሐረግ ሶስት ጊዜ ተደጋግሟል። ይሄ የሆነው ነገር የተካሄደበት ሥፍራ በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ነበር። የሆነውም ነገር እነርሱ ይሆናል ብለው ጭራሽ ያልጠበቁትና በልባቸው ካሰበቡት ሁኔታ እጅጉን የሚቃረንና እነርሱን በከባድ ኀዘንና ግራ መጋባት ውስጥ የከተተ ነበር።
ይህም የሆነው ነገር፣ "በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ

ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፤[20] **እርሱን የካህናት አለቆችና ገዦቻችን ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሰጡት፤ ሰቀሉትም።**..." በማለት ገልጠውታል፤

ይሄ ክፍል የሚያሳየን እነርሱ ጌታ ኢየሱስን የተረዱት፣ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት በተግባርና በቃል **ብርቱ ነብይ መሆኑን ብቻ** ነበር። ነገር ግን ከእርሱ በፊት በእስራኤል ምድር ተነስተው የነበሩት ብርቱ ነብያት አንዳቸውም ጌታ እንዳደረገው ከድንግል አልተወለዱም፣ ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጣሁ፣ ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ፣ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕወት ይኖራል፣ ዕውነትና መንገድ እኔ ነኝ፣ በሩ እኔ ነኝ፣ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም፤ አላሉም፤ ሞቶ ከተቀበረ አራት ቀን የሆነውን ሬሳ ከመቃብር አውጥተው በሕይወት አላኖሩም፣ ....ወዘተ። ጌታ ኢየሱሰ ከዘላለም ዘመናት በፊት አምላክ የነበረ ሆኖ ሳለ ነው የሰው ልጆችን በኀጢአት ምክንያት ከደረሰባቸው ሰቆቃ በማውጣት ለመርዳት፣ ራሱን አዋርዶ እጅግ ዝቅ ብሎ ሰው ሆኖ ወደ ምድር መምጣቱን ስላላወቁ ነው አንደ ብርቱ ነብይ ብቻ ያዩት።

የኤማሁስ መንገደኞችና ሌሎችም ብዙዎች ጌታ ኢየሱስን የደርጋል ብለው ያሰቡት እስራኤላዊያንን ከሮማዊያን ቅኝ ተገዥነት ነጻ የሚያወጣ መሪ ይሆናል ብለው ጠብቀውት እንደ ነበር ተናግረዋል። አዎን እግዚአብሔር የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ከጨቋኝ የሰው ምድራዊ መሪዎች እጅም ታድኃል፣ ወደፊትም ይታደጋል። ነገር ግን ይሄ ምድራዊ፣ ጊዜያዊና አላፊ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የላቀ ሥፍራ የሚሰጠው ለመንፈሳዊውና ለዘላለማዊው ነው። ጌታ ኢየሱስ ያመኑትን እስራኤላዊያንን ከሮማዊያን ሹማምንት አገዛዝ ሳይሆን ከኀጢአት፣ ከሥራ ሕግ፣ ከሕግ እርግማን፣ ከጭለማው ኃይላት ተገዢነትና ከዘላለም ሞት ማለትም እጅግ ከከፉ የሰው ዘር ጠላቶች ነጻ አውጥቷል፣ አሁንም ነጻ በማውጣት ላይ ነው።

ጌታ ኢየሱስን ለሞት ፍርድ አሳልፈው የሰጡትና እንዲሰቀል ያደረጉት የራሳቸው የእስራኤላዊያን ካህናት አለቆችና ገዥዎቻቸው መሆናቸውን መስክረዋል። በቀዳሚነት ለአይሁዳዊያን ከዚያም ለመላው የዓለም ሕዝብ አዳኝ ሆኖ የመጣውን ጌታ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ቁንጮ ተደርገው የሚታዩት የራሳቸው ካህናት አለቆችና ገዢዎቻቸው ገዳዩ ሆነው መገኘታቸው አእምሯቸው ምን ዓይነት ጨለማ ቢወርሰው እንደሆነ መገመት ይከብዳል። በእግዚአብሔር ላይ አንዲህ ዓይነት የጠላትነት ሥራ ከመስራት እግዚአብሔር ራሱ ያድነን።

**በዚያን ሰሞን በኢየሩሳሌም ከተማ የሆነው ነገር** በተለያዩ ወገኖች የተለያየ ስሜት ፈጥሯል። በፈሪሳዊያና ተከታዮቻቸው ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ብዙ በማሳደድ አሰቃይተውት በመሞቱ የፈለጉት ነገር ለጊዜው የተከናወነላቸውና የጌታ ሕልውና ያበቃለት ስለ መሰላቸው መደሰታቸው አይቀርም። በጌታ ተከታዮችና ወዳጆች ዘንድ ግን የሆነው ነገር እነርሱ ያልጠበቁት ስለ ነበር እጅግ በማዘን ተስፋ ከመቁረጣቸውም በላይ የአይሁድ እምነት መሪዎች ጉዳት ያደርሱብናል በማለት በታላቅ ስጋት ውስጥ ገብተው ነበር።

እነርሱን ያሳዘናቸው በጌታ ኢየሱስ ላይ የደረሰው ከባድ ስቃይና መከራ ለአሰቃቂ ሞት ያበቃው በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ያደርግልናል ብለው የጠበቁት በጊዜው ሮማዊያን ቅኝ ገዥዎቻቸው

ያደርሱባቸው ከነበረው ምድራዊ ጭቆና በመሰላቸታቸው ከዚያ ነጻ ያወጣናል ብለው ጠብቀው ስለነበር ያ ህልማቸው እውን ሳያደርግ የተለያቸው በመሆኑ ጭምር ነበር። ሉቃ 24፡21፣

ሉቃስ 24፡25-30፣ ጌታ ኢየሱስ እነዚህ የኤማሁስ መንገደኞች በእርሱ ላይ በደረሰው ነገር እጅግ እንዳዘኑ አውቆ ከገቡበት ኀዘን ሊያወጣቸውና ሊያጽናናቸው ስለነበር ወደ እነርሱ የሄደው፤ እየተጓዙ ይነጋገሩበት የነበረው ጉዳይ ጠይቋቸው ከነገሩት በኋላ እንዲህ አላቸው፤ *“እናንተ የማታስተውሉ ሰዎች፣ ልባችሁም ነቢያት የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ፣ 26 ክርስቶስ ይህን መከራ መቀበልና ወደ ክብሩም መግባት አይገባውምን?” 27 ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው።*

ሆኖም ይህ ሁሉ ቢያስረዳቸውም ከተናገራቸው ነገር የተረዱት ቢኖርም ከሃዘናቸው ግን አልተላቀቁም ነበር። በስተመጨረሻም ወደ ኤማሁስ መንደር በደረሱ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ፤ ነገር ግን ቀኑም እየመሸ ስለነበር ከእነርሱ ቤት ገብቶ እንዲያድር አጥብቀው ለምነውት ወደ ቤታቸው ገባ። አብሯቸው በማዕድ በተቀመጠ ጊዜ እንጀራውን (ዳቦውን) አንስቶ ባረከና ቆርሶም በሰጣቸው ጊዜ አይናቸው ተከፍቶ አወቁት። እርሱም እነርሱ ከገቡበት ከባድ ኀዘን እንዳወጣቸው ከእነርሱ ተሰወረ። እነዚያ እጅግ አዝነው የነበሩ የኤማሁስ ሰዎች ራሳቸው ጌታ ከሙታን ተነስቶ በዓይናቸው በማየታቸው በጣም ተደሰቱ።

እነዚህ ታላቅ ደስታ የተሰማቸው ሰዎች ያደረጉት ምንድነው?
ሉቃ 24፡33-35፣ *"በዚያኑም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ዐሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም በዚያ በአንድነት ተሰብስበው አገኟቸው፤ 34 “እነርሱም ጌታ በእርግጥ ተነሥቶአል! ለስምዖንም ታይቶአል” ይባባሉ ነበር። 35 ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም በመንገድ ላይ የሆነውንና ኢየሱስ እንጀራውን በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንዳወቁት ተረኩላቸው።"*

ይህን እየተነጋገሩ ሳሉ፣ ጌታ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። እነርሱም እንደገና ደንገጥ ቢሉም፣ ጌታ አረጋግቷቸው ደስታቸው እየጨመረ ሄደ።

በዚሁ ምዕራፍ መጨረሻ ገደማ ጌታ ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለሕዝቦች ሁሉ ንስሃና የኀጢአት ስርየት እንደሚሰበክ፤ ለዚህም እነርሱ ምስክሮች እንደሚሆኑ፤ እግዚአብሔር አብ የሰጠውን ተስፋ እንደሚልክላቸውና ኃይል እንደሚቀበሉ የምስራች ዜና ነገራቸው። ይህም ቃሉ ሌላ ተጨማሪ ደስታ የሚያላብስ ነበር። ከሕማማቱ በኋላ ራሱ ቀርቦ ሕያው መሆኑን በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸው 40 ቀንም አልፎ አልፎ ይታያቸው ነበር።

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሐዋሪያቱ ተሰባስበው ባሉበት መንፈስ ቅዱስ በኃይል ወርዶባቸው ኃይል ተቀብለው ራሳቸው ልዩ ልዩ ታምራዊ ሥራዎች ማድረግ አስችሏቸው የምስራቹን ቃል በእስራኤልና በዙሪያው ላሉ ሕዝቦች ሁሉ በመሰበክ ደስታው እየተስፋፋ ሄዶ ይኸውና ለእኛም ይህን የምስራች ዜና ደረሰን። ክብር ለእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን!!! እናንተም በጌታ ታምናችሁና ወዳችሁት የምትከተሉት ሁሉ እየጨመረና ወደ ሌሎች ሰዎች እየተስፋፋ የሚሄድ የጌታ ማነቃቃትና ደስታ ይሆንላችኋል።

ከሉቃ 24፡1-35 ድረስ ያለው ክፍል የሚያስረዳው ዋናው ነገር በዚያን ሰሞን (በ3ቱ ቀናት) በኢየሩሳሌም ውስጥ ስለ ሆነው ነገር ነው። ያ የሆነው ነገር ጌታን ይወዱ የነበሩ ሰዎች ሁሉ በከባድ ሀዘን ውስጥ የከተተ ነበር።

ጌታ ግን ይሄ የሆነው ነገር እንደሚሆን ወንጌል በእስራኤል ከተሞች እየተዘዋወረ በሰበከበት ጊዜ ሁሉ እጁ በተቃዋሚዎቹ እስከ ተያዘበት ጊዜ ድረስ እርሱ በኃጢአተኞች እጅ ብዙ መከራ ተቀብሎ እንደ ሚሞትና ከዚያም ደግሞ በሶስተኛው ቀን እንደ ሚነሳ በግልጽ አስቀድሞ ሲናገራቸው መቆየቱን ቢያንስ 13 ጊዜ ያህል በወንጌላት ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል (ሳይናገራቸው ደብቆ ያቆየው አልነበረም)። ከእነዚህ ከተመዘገቡት ውስጥ በእርሱ ላይ ከባድ መከራ የሚድሰርስበት በመሆኑ ተሰምቷቸው (ገብቷቸው) እንዳዘኑ አንድ ጊዜ ብቻ ተመዝግቧል። ማቴ 17፡22-23፤

ነገር ግን ምንም ያህል ደጋግሞ ቢነግራቸውም እነርሱ ግን የሚላቸው ነገር በውል ምን እንደሚል ሳይገባቸው የቀረ ቢሆንም መልሰው እንዲያስረዳቸው ለመጠየቅ ፈርተው ዝም ብለው እንዳለፉት ስድስት ያህል ጥቅሶች ያሳያሉ።

ጌታም በእርሱ ላይ ወደፊት የሚፈጸመው በደል ጉዳይ ደጋግሞ ሲነግራቸው እንዳልገባቸው ቢያውቅም አእምሯቸውን ከፍቶ እንዲረዱት ማድረግ ሲችል አላደረገም። እኔ ያን ያላደረገበት ምክንያት ሊሆን ይችላል ብዬ የማስበው፤ የሚደርስበት መከራ እርሱን መከተል እንደ ጀመሩ ገደማ በውል ቢረዱ ኖሮ ከእርሱ ጋር በነበሩበት ሶስት ዓመታት ጊዜ ሁሉ ኀዘንተኞች ሆነው እንዲቀጥሉና አንዳንዶቹ ከዚሁ የተነሳ እርሱን መከተል የሚተዉ ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ ለሶስት ቀናት ብቻ ግራ ቢጋቡም ከትንሳኤው ጊዜ ጀምሮ ቢያጽናናቸው በጣም ቀለል የሚል ቢሆን ነው።

እርሱ ወደ ዓለም የመጣበት ዓላማ ከእስራኤላዊያንም ሆነ ከሌሎች የዓለም ሀገራት ሁሉ በእርሱ የሚያምኑትን ከምድራዊ የአጭር ጊዜ የኑሮ ውጣውረድ ለማሳረፍ ሳይሆን ከዘላለም ሞትና ጥፋት በማዳን የዘላለም ሕይወት መውረስ እንዲችሉ ለማድረግ ነበር። ይሄ እርሱ የመጣበትና ሙሉ በሙሉ አጠናቆ በመስራት የጨረሰው ጉዳይ እነርሱ ያደርግልናል ብለው ከጠበቁት ጉዳይ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የላቀና የከበረ በመሆኑ ለጊዜው በቅኝ ገዦች ሥር ቢሆኑም በጣም ደስ ሊሰኙበት የተገባ ጉዳይ ነበር።

ሉቃ 9፡43-45፣ "…ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፣ [44] "ይህን የምነግራችሁን ነገር ከቶ እንዳትዘነጉ፤ የሰው ልጅ አልፎ በሰዎች እጅ ይሰጣልና" አለ። [45] እነርሱ ግን ይህን አባባል አልተረዱም፤ እንዳያስተውሉ ነገሩ ተሰውሮባቸው ነበር፤ መልሰው እንዳይጠይቁትም ፈሩ።

ሉቃ 18፡31-34፣ ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለብቻ ወስዶ እንዲህ አላቸው፤ "እንግዲህ ወደ ኢየሩሳሌም ልንወጣ ነው፤ ነቢያት ስለ ሰው ልጅ የጻፉትም ሁሉ ይፈጸማል። [32] ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፤ እነርሱም ያፌዙበታል፤ ያንገላቱታል፤ ይተፉበታል፤ ይገርፉታል፤ ከዚያም ይገድሉታል። [33] እርሱም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ይነሣል።" [34] ደቀ

መዛሙርቱ ግን ከዚህ ሁሉ የተረዱት አንድም ነገር አልነበረም፤ አባባሉም ተሰውሮባቸው ነበር፤ ስለ ምን እንደ ተናገረም አላወቁም። ይላል፡፡

መሲሁ ጌታ ኢየሱስ በኃጢአተኞች ምትክ ካልሞተና በሶስተኛውም ቀን ካልተነሳ የኃጢአት ስርየትና ከዘላለም ሞት መዳን የለም፡፡ የጌታ ሐዋሪያትም ሆነ ተከታዮቹ ጌታ ይህን ያህ ወሳኝ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ቃል ሲናገራቸው ያልገባቸው ክፍል እንዲያስረዳቸው አለመጠየቃቸው ያስከተለው ችግር፡፡

- ሴቶቹ በክብር ከሞት የተነሳውን ጌታ እንደ ሞተ የቀረ መስሏቸው አስከሬኑን ሊቀቡ ሽቱ ገዝተው በማዘጋጀት በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ገና ማለዳ ሳለ መቃብሩ ጋ ሄዱ፡፡ ማር 16፡1፤
- የጌታ ሐዋሪያት አይሁድ መሪዎች አደጋ እንዳይጥሉባቸው ፈርተው ተሰባስበው ያሉበት ቤት ዘግተው በመቆለፍ በኀዘን ይቀመጡ ነበር፤ ዮሐ 20፡19
- ሴቶቹ ከመቃብሩ ጋ ተመልሰው ለአስራ አንዱና አብረዋቸው ለነበሩት የጌታ ትንሳዔ ዜና ባመጡላቸው ጊዜ ግራ መጋባትና ወዲያ ወዲህ መሯሯጡ ውስጥ ገቡ፤ሉቃ 24፡11-12
- ጌታ ራሱ በተዘጋ ቤታቸው ሊያጽናናቸው ሲገባ በደስታ በመቀበል ፈንታ ምን መጣብን ብለው ይፈሩና ይደነግጡ ነበር፤ ሉቃ 24:36-38፣
- የኤማሁስ መንገደኞች የሆኑት ብዙም ታዋቂነት ያልነበራቸው የጌታ ተከታዮች ከኢየሩሳሌም 11 ኪሎ ሜትር ርቆ ወደሚገኘው ቤታቸው ተጉዘው የደረሱት በታላቅ ኀዘን ተሞልተው ነበር፡፡

ስለዚህ የአሁን ዘመን የጌታ ኢየሱሰ ተከታዮች የአግዚአብሔርን ቃል ሲማሩ በተለይ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያላቸው ክፍሎች ላይ ያልተረዱት ነገር ካለ ቃል አቅራቢውን ወይም ሌላ ሊያስረዳ የሚችል አገልጋይም ሆነ አማኝን ጠይቆ ለመረዳት አለመፍራት ነው፡፡ ዝም ብለው ካለፉት ባልጠበቁት ጊዜ ያላሰቡት ጉዳት ሊያስከትል ይችላልና፡፡

ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)      2019 ዓ.ም.